## በመከራ ጽና

በመከራ ጽና በፈተና ጽና
ለጊዜው ነው እንጂ ሁሉም ያልፋልና

እዮብ ተጨነቀ በጣም ተማረረ
በመከራው ብዛት ትግስትን ተማረ
ልጅ የሌለው ሆነ አጣ ንብረቱን
በመከራ ጸንቷል አልካደም አምላኩን

**በመከራ ጽና**

መፈተን መልካም ነው ያነጻል እንደወርቅ
በመጨረሻው ቀን በክብር እንድትደምቅ
አንዱን ሳትሻገር ሊላው ቢተካብህ
በሕይወት ዘምንህ ፈተና ቢገጥምህ

**በመከራ ጽና**

ከአምላክህ ተስማማ እራስህን አዋርድ
በቃሉ ተመራ እንደፈቃዱ ሂድ
ዋጋህ በአምላክህ ዘንድ በሰማይ አለና
በርታ ክርስቲያን ሆይ በፈተና ጽና

**በመከራ ጽና**

## ድንግል የዚያን ጊዜ

ድንግል የዛን ጊዜ የዛን ጊዜ (2) ሐዘንሽ በረታ
በመስቀል ላይ ሆኖ ልጅሽ ሲንገላታ (2)

የግፍ ግፍ ደርሶበት የዚያን ጊዜ ተጠማሁ ሲልሽ
ለውሻ ያጠጣሽ በወርቅ ጫማሽ (2)
**ድንግል የዚያን ጊዜ**

ሴቶች ሲያባርሩት የዚያን ጊዜ ራርቶ ሆድሽ
ለፍጡር በማዘን ውሃ ያጠጣሽ (2)
**ድንግል የዚያን ጊዜ**

ተጠማሁ እያለ የዚያን ጊዜ ሲናገር ልጅሽ
ታዲያ እንደምን ቻለ ወላድ አንጀትሽ (2)
**ድንግል የዚያን ጊዜ**

እንደዚያ ስታለቅሽ የዚያን ጊዜ ሀዘን ሲውጥሽ
እነማን ነበሩ ያስተዛዘኑሽ (2)
**ድንግል የዚያን ጊዜ**
ስታለቅሽ በማየት የዚያን ጊዜ ራርቶ ልጅሽ
ዮሐንስን አፅናኝ አንደ ልጅ ሰጠሽ (2)
**ድንግል የዚያን ጊዜ**